ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

በ

አሰግድ ንጉሴ

የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስረአት በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነት

13/10/2014 ዓ.ም

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቲያትር ጥበባት ትምህርትክፍል

በ

አሰግድ ንጉሴ

የጥናቱ አማካሪ

መምህር ተመስገን ሽታዬ

ለአርትስ አፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የማህበራዊ

ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ የቲያትር

ጥበባት ትምህርት ክፍል

13/10/2014 ዓ.ም

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ ።

የአማካሪው ስም _____

ፊርማ _____

ይህ ተማሪ አሰግድ ንጉሴ የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አዲባና የጋብቻ ስነ -ስረአት በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነትበሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያዲግሪ ማሟያጥናታዊፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን የጥራት ደረጃ ያሟላና ለቲያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው ። ይህም በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል ።

ፈታኝ አንድ ስም _____

ፊርማ_____

ፈታኝ ሁለት ስም _____

ፊርማ _____

ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ለድንግል ማርያም ልጅ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርእና ምስጋና አቀርባለሁ። በመቀጠል ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ እንዳዘጋጅ መረጃ በመስጠት እና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላገዘኝ ለአባቴ ለመምህር ንጉሴ እሼቴ አመሰግናለሁ ። በመቀጠል በማማከር ላገዘኝ ለመምህር ተመስገን ሽታዬ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

አበርክቶ

በብዙ ፈተና ውስጥ እኔን ደስተኛ ለማድረግ የራሷን ደስታ ለዘነጋችው ለእናቴ አስናቀች ይልማ እና ለአባቴ ለመምህር ንጉሴ እሸቴ አበረክታለሁ።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት የሚያተኩረው የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አዲባና የጋብቻ ስነስረአት በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነት ላይ ሲሆን የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስረአት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የሚዳስስ እና የሚተነትን ጥናታዊ ፅሁፍ ነው ። አጥኚው ጥናቱን ለማጥናት የተጠቀመው የጥናት አይነት ገላጭ የምርምር ዘዴ ሲሆን መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው ዘዴዎችም ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ናቸው ። ስለ አዲባና የጋብቻ ስነ-ስረአት እውቀት ያላቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና የአጥኚውን ምልከታ ተጠቅሟል ። እንዲሁም ስለ ትውፊታዊ ተውኔት የተፃፉ መፅሀፍትን እና ጥናታዊ ፅሁፎችን በመዳሰስ ጥናቱ ተጠንቷል።

ሙዳየ ቃላት

ሲቆ(siqoo).....የጋብቻን ፍላጎት የምታሳይ አጭር ብትር።

ሚልኪ(milki).....በድምጿ ጥሩ ና መጥፎውን ለመለየት የምታገለግል ወፍ።

ሳማጤ(saamaxe).....ፀጉር ላይ ተደርጎ ወደ ኋላ የሚንጠለጠል
የልጃገረድነት ምልክት።

ካሌ(kalle).....ከቆዳ ከጨሌ የሚሰራ የልጅ ማዘያ።

አዲባና(addiibaana).....በሴት ልጅ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የጋብቻ ስነስረአት።

ሐዋዲ(hawadii).....በመተጫጨት የሚደረግ የጋብቻ አይነት።

ከዳ(kadhaa).....ቤተሰብ ልጃችሁን ለልጃችን ብለው በልመና የሚፈፀም
የጋብቻ ስነ-ስረአት ነው።

ቡታ(butaa).....በጠለፋ የሚፈፀም የጋብቻ ስነ-ስረአት።

ቆራሱማ(Qoraassuuma).....(ወይራጭስ) የወተት መአዛ ጥሩ እንዲሆን
የሚያደርግ።

ሚኢ(mi'ii).....ትኩስ ወተት ።

ኦኮቴ(ookotee).....ከሸክላ የተሰራ የውሃ መቅጃ (እንስራ) ።

ቦሮ(borro)..... የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ ባህላዊ ልብስ

ማውጫ

ርዕስ
ገፅ

ምስጋና i
አበርክቶ ii
አጠቃሎ iii
መዳየቃላት iv
ምዕራፍ አንድ 1
1.1 መግቢያ 1
1.2 የጥናትዳራ 1
1.3 የጥናቱአላማ 1
1.3.1 አብይአላማ 2
1.3.2ንዑስ አላማዎች 2
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 2
1.5 የጥናቱመጠነ ርዕይ 2
1.6 የጥናቱ አወቃቀር 2
1.7 የጥናቱ ዘዴ 3
1.7.1 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ 3
1.7.1.1 ቃለ-መጠይቅ 4
1.7.1.2 ምልከታ 4
1.8 በጥናት ወቅት ያጋጠመ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች 5
1.9 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች 5
ምዕራፍ ሁለት 5
2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት 6
2.1.1 የተውኔት ምንነት 6
2.1.2 የትውፊታዊ ተውኔት ምንነት 7
2.1.3 የትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን 8
2.1.3.1 የመከወኛ ቦታ (መቼት) 9

2.1.3.2 ቃለ-ተውኔት 10
2.1.3.3 ቁሳቁስ 11
2.1.3.4 አልባሳት 12
2.1.3.5 ታሪክ 13
2.1.3.6 ሚና ክፍፍል 14
2.2 የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት 16
ምዕራፍ ሶስት 17
3. የመረጃ ትንተና 17
3.1 የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ መልካ ምድራዊ ዳራ 17
3.2 የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የጋብቻ አይነቶች 17
3.2.1 አዲባና (addi baana) 18
3.2 2 ሐዋዲ (hawaddii 20
3.2.3 ከዳ (kadhaa) 21
3.2.4 ቡታ (buttaa) 22
3.3.የአዲባና ጋብቻ ስነ-ስርአት በትውፊታዊ ተውኔት ምንነት 23
3.3.1መቼት 23
3.3.2 ቁሳቁስ 24
3.3.3 ግብአተ ድምፅ 25
3.3.4 አልባሳት 26
3.3.5 ውዝዋዜ 27
3.3.6 ሚና ክፍፍል 28
3.3.7 የመጠጥእና የአመጋገብ ስነ-ስርአት 29
3.3.8 ዘፈን 30
ምዕራፍ አራት 33
4.1 ማጠቃለያ 33
4.2 የመፍትሔ ሀሳብ 34
ዋቢ መፅሀፍ
አባሪ

ምዕራፍ አንድ

1.1 መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በቋንቋ፣ በባህል፣ በሀይማኖታዊ ስርአቶች፣ አመታዊ ክብር በአላት፣ ሀገር በቀል በሆኑ እውቀቶች ህዝብን የሚመሩ ባህላዊ የአስተዳደር ስርአቶችን ዘርግታ ትጠቀማለች።።ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ከ80 በላይ ከሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ አንዱ ነው።።የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በደቡባዊ ኦሮሚያ ነው።።የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በሁለት ዞኖች ውስጥ ይኖራል።። ምዕራብ ጉጂ ዞን እና ምስራቅ ጎጂ ዞን ይባላሉ።። የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ የሚኖርበት የመሬት አቀማመጥ ኮረብታማ ሲሆን ቆላ፣ ደጋ፣ ወይናደጋ፣ የአየር ንብረት አለው።።የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ ባህላዊ ክዋኔዎች አሉት።። የጋብቻ ስነ-ስርአት፣ የለቅሶ ስነ-ስርአት፣ የገዳ ስነ-ስርአትን ይጠቀማል።። በጉጂ ኦሮሞ አራት አይነትየጋብቻ ስነ-ስርአቶች አሉ ፤ አዲባና፣ ሐዋዲ ፣ ቡታ ፣ ከዳ ይባላሉ ።አጥኚው የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአትን በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነት አጥንቷል ።።

1.2 የጥናትዳራ

አጥኚው ይህን የጉጂኦሮሞ ብሔረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነት አጥንቷል።።የጋብቻው ስነ-ስርአት ውስጥ ሴቶች በፍላጎታቸው የመረጡትን (የወደዱትን) ወንድ አዲባና ስነስረአት ንተጠቅመው ማግባት ይችላሉ። የጉጂ ብሄረሰብ ለሴቶች የሰጠው የመብት እኩልነት እና አጥኚው ባህሉ እንዲታወቅ ካደረበት ፍላጎት የመነጨ ሲሆን መረጃ ለማስቀመጥ ጥናቱን አጥንቷል።

1.3 የጥናቱ አላማ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በውስጡ አብይና ንዑሳን አላማዎችን አካቶ ይዟል።።

1.3.1 አብይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና አላማ የጉጂኦሮሞ ብሔረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአተ በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነት ማቅረብ ነው።

1.3.2 ንዑስ አላማዎች

- ✓ በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስረአትን መግለፅ ፡
- ✓ የጉጂ ኦሮሞ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት እንዴት እንደሚከወን ማሳየት።

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

- ✓ በጉጂኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ዙሪያ ጥናት ማጥናት ለሚፈልጉ አካላት እንደ ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፍ በመሆን ያገልግላል።
- ✓ የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ አዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአቱን ወደ ፊልም፣ ቲአትር፣ ዘጋቢ ፊልም መቀየር ለሚፈልጉ ባለሞያዎች እንደ መረጃ መጠቀም ያስችላል።
- ✓ የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ ውስጥ እየኖሩ ባህሉን ለዘነጉ የብሄረሰቡ አባላትእና ከባህሉውጪላሉየማህበረሰብ ክፍሎች ባህሉንአንዲያውቁት ያደርጋል ።እንዲሁም እንዲጠብቁት ያደርጋል።

1.5 የጥናቱ መጠነ ርዕይ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት የሚያተኩረው የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነት ተንትኗል።

1.6 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው።በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ መጠነ ርዕይ፣ አብይ እና ንዑስ አላማ ፣ የጥናቱ አወቃቀር ፣ የጥናቱ ዘዴ፣ በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሄ ሀሳቦች ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎችን ይዟል፡ ፡ በምዕራፍ ሁለት፣ የንድፈ ሀሳብ ቅኝት፣ የተውኔት ምንነት፣ የትውፊታዊተውኔት ምንነት፣ የትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን ፣ መቼት፣ ቃለ ተውኔት ፣ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ ታሪክ፣ ሚና ክፍፍል፣ የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝትን አካቷል። በምዕራፍሶስት፣ የመረጃ ትንተና የጉጂ

ኦሮሞ ብሔረሰብ ዳራዊ ቅኝት፣ የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የጋብቻ አይነቶች ፣ አዲባና፣ ሀዋዲ፣ ከዳ፣ ቡታ፣ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በትውፊታዊ ተውኔት ምንነት፣መቼት ፣ ቁሳቁስ፣ ግብአተድምዕ ፣አልባሳት ፣ ውዝዋዜ ፣የሚናክፍፍል ፣ የመጠጥእናየአመጋገብስነስረአት ፣ ዘፈንንአካቶይሟል። በምዕራፍ አራት ፣ማጠቃለያ፣ የመፍትሔ ሀሳብ፣ ዋቢ መፅሀፍት ፣ አባሪን አካቶ ይሟል።

1.7 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል ። ምክንያቱም በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ውስጥ ያሉትን ትውፊታዊ ክንውኖች ልንገልፅ የምንችለው ትንታኔ በመስጠት እና በማብራራት ነው ። አለም እሸቱ <<መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ>>በሚለው መፅሀፉ ስለ ገላጭ የምርምር ዘዴ የሚከተለውን አስፍሯል።

ገላጭምርምር ገለፃን ትንታኔን እና አተረጓጎምንመሰረት

የሚያደርግ ሲሆን በሁለትተለዋዋጮች መካከል

የሚኖረውን ተዛምዶእያወዳደረና እያነፃፀረ ሊመለከት

ይችላል። በዚህ ሂደት ውስጥ መረጃዎችንከተለያዩ

ምንጮች የሚያሰባስብ ሲሆንትኩረቱን ግን የአንዱን

ተጨባጭ ሁኔታትክክለኛ ባህሪ መግለፃፅ ወይም

ማሳወቅይሆናል።(1994፣148-149)

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ ስለ ትውፊታዊ ተውኔት የተፃፉ መፅሃፍትን በማንበብ ፣ ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎችን ቅኝት በማድረግ እና ቃለ መጠይቅ ፣ ምልከታን በመጠቀም ጥናቱ ተጠንቷል ።

1.7.1 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታን መረጃ ለመሰብሰብ ተጠቅሟል ።

1.7.1.1 ቃለ-መጠይቅ

ቃለ-መጠይቅ አንድ ጥናት የሚያጠና ጥናት አድራጊ በጥናቱ ወቅት ስለሚያስፈልገው መረጃ፣ እውቀትና ግንዛቤና ልምድ ያላቸውን ሰዎች በቃለ መጠይቅ የሚገኝ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው ። አለም እሸቱ "መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ"በሚለው መፅሀፉ ስለ ቃለ መጠይት የሚከተለውን አስፍሯል ።

ቃለ-መጠይቅ ተጠያቂው ከጠያቂው ጋር

በግንባር ተገናኝቶ በጽሁፍ ሳይሆን በቃል

መልስ የሚሰጥበት ሂደት ነው። ቃለ-

መጠይቅ በብልሃት ከተያዘና ተግባር ላይ

ከዋለ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያና

ማጠናከሪያ ስልቶች በተሸለ መንገድ መረጃ

ለማሰባሰብ ያስችላል። (1994፣65)

አጥኚው በቃለ-መጠይቅ ጥናቱን የሚያጠናው የጉጂኦሮሞ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ በመሆን በአብዛኛው መረጃ የሚገኘው በባህሉ ውስጥ ስላደጉና ስርአቶቹ ሲከወን ተሳታፊ የነበሩ ሰዎችን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ግልፅ መረጃ ስለሚያስገኝ ከጥናቱ የቃለ-መጠይቅ ዘዴን ተጠቅሟል ።

1.7.1.2 ምልከታ

በምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥናት አድራጊው ጥናቱን ሊያካሂድ በተገኘበት ቦታ በእይታውውስጥ የሚገቡ መረጃዎችን የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀምይሰበስባል ። አለም እሸቱ <<መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ >>በሚለው መፅሀፍ ውስጥ ሰለ ምልከታ የሚከተለውን አስፍሯል ።

መሰረታዊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሲባል የሚከናወን ትኩረት

እና ምርምር የሚደረግ ምልከታ በአለፍ አገደም አይተን የምናልፈው

ጉዳይ ሳይሆን በቅድሚያ ብዝመረጃ ማሰባሰቢያ ስልት ነው ። (1994 ፣ 69)

በምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥናት አድራጊው እይታው ውስጥ የገቡ መረጃዎችን በፅሁፍ ማስታወሻ በመያዝ ፣ ፎቶ በማንሳት ፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማስቀረት እንዲሁምድምፅ መቅጃን በመጠቀም መረጃ ሰብስቧል ።

1.8 በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች

የአዲባና የጋብቻ ስነ ስረአት ይበልጥ ቅርበት ያላቸው ሰዎች በጉጂ አከባቢ በተፈጠረው የሰላም መደፍረስ ምክንያት ስጋት ስላደረባቸው መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን አጥኚው ገጥሞታል ።እንደ መፍትሄ የተጠቀመው በሌሎች አከባቢዎች ፍቃደኛ ግለሰቦችን ለጥናቱ መረጃ እንዲሰጡት በማድረግ ተጠቅሟል።

1.9 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- ✓ የጉጂኦሮሞ ብሔረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ - ስረአትምንነት ?
- ✓ የጉጂኦሮሞ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ቅደም ተከተላዊ ሂደት እንዴት ይካሄዳል?
- ✓ የጉጂኦሮሞ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ እንዴት

ምዕራፍ ሁለት

2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

2.1.1 የተውኔት ምንነት

ተውኔት የአንድ ማህበረሰብ ባህሪ፣ ሀይማኖታዊ ስርአቶች፣ ባህላዊ እሴቶችን አቅፎ የሚይዝ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ ተውኔት የገሀዱ አለምየህይወት ተግባራትን እየቀዳ በቦታ እና በጊዜ ተገድቦ ለተመልካች የሚቀርብ ታሪክ ነው፡፡ ተውኔት ማድረግን ወይም መተወንን ያመለክታል፡፡ ተውኔት በፅሁፍ እና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ የማህበረሰብ ታሪኮችን በጊዜና በቦታ ተገድቦ በመድረክ ቲአትር ያቀርባል፡፡ ዘሪሁን አስፋው ‹‹የስነ-ፅሁፍ መሰረታዊያን›› በተሰኘው መፅሐፍ የተውኔት ምንነት እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> ተውኔት የራሱ ባህሪያት ያሉት አንድ የስነ-ፅሁፍ ዘር ሲሆን እንደ ሌሎቹ የስነ-ፅሁፍ ዘሮች የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገጽታዎች ያንፀባርቃሉ፡፡የተመረጠን የማህበረሰብ ገፅታ በማሳየት ረገድ ከሌሎቹ የስነ-ፅሁፍ ዘሮች የሚጋራቸው ኪነ-ጥበባዊ ባህሪያት ቢኖሩትም ገና ከመነሻው በተዋንያን አማካኝነት ከመድረክ ላይ እንዲቀርብ የሚደረስ በመሆኑ ከሌሎቹ በአያሌው የተለየ ነው፡፡ ተውኔት በደራሲው ወይም በፀሀፊ ተውኔት በተመረጠ ጠባብ ቦታና የጊዜ ክልልህይወትን በድርጊት በመድረክ ላይ ስለሚያቀርብ ከቀሩት የስነ-ፅሁፍ ዘሮች ይበልጥ ለስሜታችንቅርብ ነው፡፡ (2005፣161)

ተውኔት እንደ ልቦለድ፣ግጥም፣ ወግ፣ መጣጥፍ በፅሁፍ ብቻየሚቀርብ አይደለም፡፡ በደራሲው ምናብ ውስጥ የተፈጠረውን ታሪክ በተዋንያን አማካኝነት ገፀ-ባህሪያቱን ተላብሰው ሲጫወቱ ተመልካች በመድረክ ላይ ይመለከታል፡፡ ተውኔት አለም ላይ የሚታየውን የህይወት ውጣ ውረድ ማግኘት፣ ደስታ፣ ሀሰን፣ መኖር መሞት የህይወት መንገዶችን ለመድረክ እንዲበቃ በማድረግ

ለተመልካች ያቀርባል፡፡ ተውኔት የሰው ልጅ ምድር ላይ ከሚኖረው የህይወት ቆይታ እየተቀዳ ለራሱ ለሰው ልጅ በመድረክ ላይ ይቀርባል፡፡ ተውኔት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ መጥፎ የሚባሉ ድርጊቶችን ስርቆት፣ ማታለል፣ ክፋት፣ ምቀኝነት ፀያፊ ተግባራት መሆናቸውን በተውኔት ውስጥ ያሳያል፡፡ በተቃራኒው በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን ተግባራት ሀቀኝነት፣ ታማኝነት፣ ታላቅን ማክበር ለሌሎች ክብር መስጠትን ያስተምራል፡፡

2.1.2 የትውፊታዊ ተውኔት ምንነት

ትውፊታዊ ተውኔት የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ወግ፣ ልማድ የአመጋገብ፣ የስራ ባህል፣ ልማዳዊ ድርጊት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የለቅሶ ስነ-ስርአት የእርቅ ስነ-ስርአቶችን ላይ ተመርኩዞ ይቀርባል፡፡ የትውፊታዊ ተውኔት አዘጋጅ የማህበረሰቡን እሴት የሚገልፁ ባህሎችን ማህበረሰቡ አምኖ ሊቀበለው የሚችል እንዲሁም ባህሉ ወደ ተውኔት ተቀይሮ ለተመልካች በሚቀርብበት ጊዜ የባህሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ የሚሳተፍበት ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡ የትውፊታዊ ተውኔት አዘጋጅ ከባህሉ ውጪ የሆት ድርጊቶችን በራሱ ፍቃድ መጨመር አይችልም፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት አብዛኛውን ጊዜ በመድረክ ሳይሆን ክፍት እና ሰፊ በሆነ ስፍራ ላይ ይቀርባል፡፡ ፋንታሁን እንግዳ፡፡ ተውኔታዊ መዝገበ-ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ፡፡ሀ፡፡ እስከ ፡፡ፐ፡፡ ፡፡በተሰኘው መፅሀፍ ስለ ትውፊታዊ ተውኔት እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

ከህዝባዊ ልማዶች እምነቶች ክብር በአሎች እና ስነ-ቃሎች

ላይ ተመስርቶ የሚመደረክ ባህላዊ ትርኢት ነው፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት

በፅሁፍ የሚቀመጥ ጽሁፍ ተውኔት የለውምከትውልድ ወደ ትውልድ

በቃል እየተላለፈተሰሚነት ይቀርባል፡፡

1. የትውፊታዊ ተውኔት ተመልካች ራሱ የትርኢቱ አካል አድርጎ በመቁጠር
2. የትውፊታዊ ተውኔት ትርኢት የሚቀርበው በመደበኛ ቤት ተውኔት ሳይሆን

   በገላጣ ስፍራ ነው፡፡

3. የትውፊታዊ ተውኔት ገፀ-ባህሪያት ሁሉም አስተኔ ናቸው፡፡
4. ትውፊታዊ ተውኔት በመዝሙር እና በውዝዋዜ ይታጀባል፡፡

5. በትውፊታዊ ተውኔት ጥቅም ላይ የሚውሉየመድረክ ቁሳቁሶች ባህላዊ

ከበሮዎች ጭንብሎች እናየመሳሰሉት ናቸው።

6. ከዚህ በተጨማሪ ትውፊታዊ ተውኔት ቁርጥራጭ ትዕይንቶችን የሚያገኝ

ተራኪ ያጠምዳል። (1993፣57-58)

ትውፊታዊ ተውኔት በማህበረሰብ መካከል ትኩረቱን የሚያደርግ እና ማህበረሰቡን ከሚጠቀምባቸው ቁሳቁስ፣ አላባሳት እንዲሁም የየእለት ተግባራት ተነስቶ ለራሱ ለማህበረሰቡ ይቀርባል። ትውፊታዊ ተውኔት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የሚያስተምረው በቃል በሚነገር ታሪክ በመሆኑ በተውኔት ተቀይሮ በሚቀርብበት ጊዜ ቃለ-ተውኔት ላይ ትልቅ መልዕክት ያዝላል። ትውፊታዊ ተውኔት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያላቻ ጋብቻ፣ ጠላፋን ጉዳቱን ይጠቁማል። የትውፊታዊ ተውኔት የመከወኛ ቦታ ገላጣ ስፍራ በመሆኑ ለማህበረሰቡ ቅርብ በመሆን ከማህበረሰቡ ውስጥ መሰተፍ ለሚፈልጉ ሰዎች በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጋል። የትውፊታዊ ተውኔት ገፀ-ባህሪያት ቀለል ባለ መንገድ ስለሚሳሉተመልካች የማህበረሰቡን ባህል ባልተወሳሰበ ታሪክ ውስጥ እንዲረዳ ያደርገዋል።

2.1.3 የትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን

ትውፊታዊ ተውኔት የራሱ የሆነ የተውኔት አላባውያን አሉት። በትውፊታዊ ተውኔት የሚሰራ የተውኔት ታሪክ እውነተኛ ተአማኒ ነው። ትውፊታዊ ተውኔት መሰረታዊ የሆኑ አላባዎችን ያካተተ ሲሆን እንዲሁም እንደ ሌሎቹ የተውኔት ዘውጎች ሙሉ በሙሉ የመድረክ ተውኔታዊ ስር-አቶችን አይጠብቅም። የትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን ከሌሎች የቲአትር አላባውያን ጋር የሚያመሳስሉት ቢኖርም የራሱ መለያ የሆኑ አላባዎችን አካቶ ይዟል። አዲሳለም አስቻለው ‹‹ ንግስት ዘውዲቱ ታሪካዊ ተውኔት›› በተሰኘው መፅሀፍ የትውፊታዊ ተውኔት አላባውያንንእንደሚከተለው አስፍሯል።

የመከወኛ ቦታ (Setting) ፣ ቃለ ምልልስ (dialoge)፣

አልባሳት (Costume)፣ አካላዊ ምላሽ (physical፣

Response)የሚና ክፍፍል (Role division)፣

ቂሳቁስ (cult objects) እና ቅፀላ ወይም

ምስላ (Imitation) ናቸው። (2010፣3)

አንድ ተውኔት ትውፊታዊ ተውኔት ለመባል ከላይ የተጠቀሱትን አላባዎች ማካተት አለነት። እነዚህ የትውፊታዊ ተውኔት አለናውያን የአንድን ብሄረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ልማዳዊ ድርጊት፣ ሀይማኖታዊ ስነ-ስርአቶች፣ የጋብቻ ስነ-ስርአቶች፣ የቀብር (የለቅሶ) ስነ-ስርአቶችን፣ ልማዳዊ ድርጊቶችን ተውኔታዊ ፈጠራን ባማከለ መልኩ ግብአቶችን በማካተት ቂሳቁስ፣ አልባሳት፣ ቃለ-ምልልስ፣ የመከወኛ ቦታ፣ ሚና ክፍፍሉ የባህሉን ምንነት በሚያስረዳ መልኩ ያቀርባል።

2.1.3.1 የመከወኛ ቦታ (መቼት)

መቼት የድርጊት መከወኛ ቦታና ጊዜን የሚያመለክት ሲሆንማህበራዊእውነታየተውኔቱን ድባብ፣ ዘውግ ይጠቁማል። ድርጊት በሚፈፀምበት ቦታ የሚቀርበው ተውኔትን የማህበረሰቡን ባህል ይገልፃማል። የተውኔት ድርሰት ውስጥ አጠቃላይ የድርጊቱ መከወኛግዜና ቦታ እና አነስተኛ ድርጊቶች ይከወንባቸዋል፤ ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ፐ›› በተሰኘው መጽሀፍ ስለ መቼት ምንነት እንደሚከተለው አስፍሯል።

መቼትን መቼት የሚያሰበው የድርጊቱ ቦታና ድርጊቱ

በተፈፀመበት ጊዜ ያለው ማህበራዊ እውነት ናቸው።

በአጠቃላይመቼት በአንድ በተወሰነ ተውኔታዊ ድርጊት

ውስጥ የሚገኘው ትልቁ የድርጊት መከወኛቦታ ነው።

መቸት ውስጥ የሚገኝትንሹ የድርጊት ጊዜና ትንሹ የድርጊት

መከወኛ ቦታ ነው። አብዛኛውንጊዜአጠቃላይና ውስን

የመቼት አይነቶች በአንድ ተብራርተው ተገልፀው ይቀመጣሉ።(1993፣25)

መቼት የአንድ ማህበረሰብን የአኗኗር ሁኔታ ጠቋሚ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። የበጋ፣ የክረምት ጊዜያትን ግልፅ ያደርጋል። በደራሲው እንደሚያከናውኑት ድርጊት ትክክለኛ የማህበረሰቡ ባህላዊ ክንውኖች ባህሉ ያለውን ተጨባጭ የሆኑ የጋብቻ ስነ-ስርአቶች፣ የቀብር ስነ-ስርአቶች፣ የአምልኮ

ሁኔታዎች ማህበረሰቡ በሚከናወኑ መንገድ ይቀርባሉ፡፡ ሳሙኤል ተስፋዬ‹‹የመድረክ ጀርባ ጥበባት›› በተሰኘው መፅሀፍ ስለ መቼት እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

መቼት የተውኔት ታሪክ የሚከናወንበት ቦታና

ታሪኩ የሚከወንበት ጊዜንና ማህበራዊ እውነታን

አጠቃልሎ የያዘዘ ነው፡፡ አብዛኛው ፀሀፊ

ተውኔቶች ተውኔታቸውንመፃፍ ሲጀምሩ

የሚያስቀድሙት ነገር የታሪኩን ቦታና ጊዜ

ማህበራዊ እውነታን በማስተዋወቅ ነው፡፡

ይህ ደራሲው የሚሰጠን አለም አብዛኛውን

ጊዜ ከምናውቀው ገሀድ አለም የተመሳሰለ

ነው፡፡ (2012፣131)

መቼት ጠቃሚና በተውኔት ውስጥ ጉልህ ሚና ያለው ሲሆን በፀሀፊ ተውኔት ታሪክ ውስጥ አጠቃላይ፣ ውስን፣ የጊዜ፣ የቦታ ማህበራዊ እውነታን በአንድ ላይ አካቶ የያዘ ነው፡፡ በአጠቃላይ መቼት ውስጥ ደራሲው በፈጠራው ታሪክ ውስጥ ያለው ትልቁ የድርጊቱ መከወኛ ቦታ ነው፡፡ ሀገር፣ ዘመን፣ የፖለቲካሁኔታ፣ ሀይማኖታዊ ስርአትን ያጠቃልላል፡፡ በውስን መቼት ውስጥ በደራሲው ታሪክ ውስጥ ባሉ አነስተኛ የቦታና የጊዜ ሁኔታ ማህበራዊ እውነታን ጨምሮ የያዘ ነው፡፡

2.1.3.2 ቃለ-ተውኔት

ቃለ-ተውኔት ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ገፀ-ባህሪያት የሚያደርጉት የእርስ በእርስ ንግግር ሲሆን የአንድን ተውኔት ጭብጥ፣ መቼት፣ ሴራ፣ ታሪክ ፣ የገፀባህሪያት ማንነት ምን እንደሆነ የሚያሳውቅ የተውኔት አላባ ነው፡፡ ቃለ- ተውኔት የገፀ-ባህሪያቱን ግንኙነት ይገልፃል፡፡ ሳሙኤልተስፋዬየመድረክጀርባጥበባትበሚልርዕስ ባሰሳተመው መፅሀፍ ስለ ቃለ-ተውኔት የሚከተለውን አስፍሯል፡፡

ቃለ ተውኔት የገፀ ባህሪውን ውስጣዊና ውጫዊ

ማንነት ፣ ግልፅ እና ድብቅ ስብእናውን ፣ ሀይማኖቱን ፣

ፍልስፍናውን ፣ሽንፈቱን ፣ድክመቱን ፣ ብርታቱን ድሉን

የየት ሀገር ሰው እንደሆነ ምን አይነት አለባበስ

እንደሚያዘወትርየስራውን አይነት ማህበራዊ

ደረጃውን ባህሉን ወግልማዱን ወዘተ በቃለ

ተውኔት ውስጥ ልናገኛቸው እንችላለን ።(2012 ፣ 197)

ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ውስጥ በሚፈጥሩት ተውኔታዊ ቋንቋ የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን ከመግለፅ በተጨማሪ ስራ ተውኔቱ ምንነትእና ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ተመልካች በቀላሉ እንደረዳ ያደርጋል። ቃለ- ተውኔት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡ ፡ የገፀ-ባህሪያቱን የኑሮ ደረጃ፣ የስራ ድርሻ፣ ውስጣዊ አስተሳሰብ፣ የተሳሉበትን መንገድ፣ ማህበራዊ መስተጋብራቸውን በተውኔት ውስጥ ያሳያል ።

2.1.3.3 ቁሳቁስ

ቁሳቁስ የተውኔት ድባብ ማሳያ ሲሆኑ ተመልካች የታሪኩን ጉዘት እና ንባራዊ ሁኔታን በቀላሉ እንዲረዳ ያደርጋል። የገፀ-ባህርያትን ማንነት ለመግለፅ እንዲያስችላቸው በተውኔት ውስጥ ይካተታሉ። ትውፊታዊ ተውኔት በሚቀርብበት ጊዜ ማንኛውም መገልገያ ቁሳቁስ ይባላሉ። የቁሳቁስ አይነቶች በእጅ የሚያዙ፣ መድረክ ላይ የሚቀመጡ፣ ግድግዳ ላይ የሚሰቀሉ ናቸው። መሳሪያ፣ ጦር፣ መጠጫ፣ መመገቢያ እቃዎች፣ ማበጠሪያ በእጅ የሚያዙ የእለት ተእለት የድርጊት መከወኛ ቁሶች ናቸው። መድረክ ላይ የሚቀመጡ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ቁም ሳጥን፣ መደርደሪያ ናቸው።ፎቶዎች፣ ጋሻና ጦር፣ ጥቅሶች መሰል ቁሳቁሶች ግድግዳላይ የሚሰቀሉ ተውኔት ቆሶች ናቸው። ፋንታሁን እንግዳ‹‹ ተውኔታዊ መዝገበ-ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ‹‹ሀ›› እስለ ‹‹ፐ›› በሚለው መፅሀፍ ውስጥ ስለቁሳቁስ አይነቶች እንደሚከተለው አስፍሯል።

አራት ክፍሎች አሉት። በአንደኛው ደረጃየመድረክ

ቁስ የሚባሉት ተዋንያንመድረክ ላይ በእጃቸው

ሳህየሚይዟቸው እንደ ደብዳቤ፣ ብርጭቆ፣ ን፣

የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የመድረክትዕይንቱ አካል በመሆን

የሚቀርቡ እንደመቀመጫ፣ ወንበር፣ አልጋ፣ ቁምሰሳጥን

ማቀዝቀዣ የመሳሰሉት እንዲሁም የመድረክ ቁሳቁስ ይባላሉ፡፡

ከዚህ ሌላ የግድግዳጌጦች ለመምሳሌ እንደ ሚለጠፉ ስዕሎች

የመስኮት መጋረጃዎች፣ የግድግዳ መስታዎትዎች እና የመሳሰሉትም

የመድረክ ቁሳቁሶች ናቸው፡፡ (1993፣85)

ቁሳቁስ በመድረክ ተውኔት ውስጥ ተውኔታዊ ጠቀሜታ አላቸው፡፡የሚሰራው ተውኔት ላይ የሚጫወቱ ገፀ-ባህሪዎች ለመድረክ አጠቃቀም የሰውነት እንቅስቃሴን ምክንያታዊ ከማድረግ፣ የመድረክ እንቅስቃሴዎች ላይ አሳማኝነትን ለመፍጠር ቁሳቁስ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ውስጥ ያላቸውነ ድርሻ የሀብት መጠን፣ ሀይማኖታዊ ምልከታን በውስጣቸው የሚያስቡትን ደግነት፣ ቅንነት፣ ክፋት፣ ምቀኝነት፣ ተንኮልን በሚጠቀሙት ቁስ ይገለፃሉ ።

2.1.3.4 አልባሳት

አልባሳት በተውኔት ውስጥ የሰውነት አካላትን መሸፈን ብቻ ሳይሆን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ አልባሳት ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ውስጥ ያላቸውን የታሪክ ድርሻ መግለፅ የሚችል የተውኔት አላባ ነው፡፡ አንድ ገፀ-ባህሪ በመድረክ ላይ የሚጠቀመው አልባስ የኑሮ ደረጃውን፣ የሚከተለውን ሀይማኖት፣ የተወለደበትን ብሄር፣ ፖለቲካዊ አስተሳሰቡን፣ ውስጣዊ ማንነትን በአልባሳት መግለፅ ይቻላል፡፡ ለቅሶ ላይ የተገኘ ሰው ነጭ በነጭ የሆነ ልብስ ለብሶ ቢገኝ በሀገራችን ባህል መሰረት ነጭ ልብስ መደሰትን እንጂ ማዘንን ስለማይገልፅ ይህ ሰው ተቃውሞ ያስተነግዳል፡ ፡ ሳሙኤል ተስፋዬ ‹‹ የመድረክ ጀርባ ጥበባት›› በሚለው መፅሀፍ ውስጥ ስለ አልባሳት የሚከተለውን አስፍሯል፡፡

በቲአትር ጥበብ ውስጥ አልባሳትሰፊ ትርጉም የያዘ

ጥበብ ሆኖ እናገኘዋለን ።በመሆኑም አልባሳት የምንላቸው

ሁሉምየሚለበሱ ነገሮችን አጠቃሎ የያዘ ሲሆንተዋንያን

ከውስጥ የሚለብሷቸው ልብሶከላይ የሚደርቧቸው ልብሶች

ፀጉራቸው ላይ የሚያስሯቸው ሻሾች፣ አንገታቸው ላይ የሚያደርጉት

ስካርቭ ትክሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉትሻርፕ(ነጠላ)፣ ጋቢ

በራሳቸው ላይ የሚያደርጉትክፍያዎች፣ ዘውዶች ፣ አክሊሎች፣ ቆቦች፣

ጥምጣሞች፣ እና መሰል ነገሮች በሙሉ አልባሳት ዝርዝር

ውስጥ ይመደባሉ። (2012፣ 100

አልባሳት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የገፀ-ባህሪያቱን ማነት እንዲሁም በሚቀርበው ተውኔት ውስጥ የኑሮ ደረጃን ፣ የወደፊት ተስፋን ፣ ፍቅርን ፣ ክብርን መግለፅ ይችላል ።

2.1.3.5 ታሪክ

ታሪክ አንድ ደራሲ ምናቡ ተጠቅሞ ጊዜ ቦታን ማህበራዊ እውነታን ባማከለ መልኩ ድርጊቶችን መጀመሪያ፣ መሐል፣ መጨረሻን ያካተተ ቅደምተከተሉን በመጠበቀ መልኩ የማህበረሰቡን ባህል፣ ወግ፣ ታሪክ፣ ሀይማኖታዊ፣ የጋብቻ፣ የለቅሶ (የቀብር)፣ አምልኳዊ ስነ-ስርአቶችን የሚያስተምር ነው።ታሪክ ያለፈ ዘመንን አጥርቶ የሚያሳይ እና ዛሬ ላይ ያለንበትንእንድንገነዘብ ያደርጋል። ፋንታሁን እንግዳ ‹‹ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ‹‹ሀ›› እስከ ፐ›› በሚለው መፅሀፍ ላይ ስለ ታሪክ እንደሚከተለው አስፍሯል።

ማነኛው ተውኔታዊ ድርጊት ወይንም ክንዋኔ በጊዜ

ቅደም ተከተል ተዘርዝሮ የሚቀመጥ ነው። ታሪክ

በጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ከአንዱ ድርጊት

ቀጥሎ የትኛው ድርጊት እንደሚከተል ለማሳወቅ

ይጠቅማል፡፡ ታሪክ የክዋኔዎች ስብስብ በመሆኑ ለ

ማነናውም የፈጠራ ስራ ማለትም ለተውኔት ለረጅም

ልቦለድ፣ ለአጭር ልቦለድ፣ ለፊልም፣ ለተራኪ ግጥም

እና ለልዩ ልዩ ተረቶች መሰረት ነው ተብሎ

ይታመናል፡፡ (1993፣55)

ታሪክ የተውኔት ክንውንን ባማከለ መልኩ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በተብራራ ሁኔታ ይቀመጣል፡ ፡ ታሪክ በተውኔት ውስጥ የድርጊት ቅደም ተከተልን ጠቋሚ ነው፡፡ በተውኔት ውስጥ እና በሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች፣ ልቦለድ ፣ወግ፣ ፊልም ውስጥ ታሪክ መሰረታዊ አላባ ሆኖ ይገኛል፡፡ ታሪክ በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የአንድ ብሔረሰብ ባህል የሚያጎላ ለብሔረሰቡ መለያ በመሆን የማንነት መግለጫ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ታሪክን ለማወቅ እና ወደ ተውኔት ለመቀየር የታሪኩ ባለቤት ጋር በመቅረብ ታሪክ አዋቂዎችን በመጠየቅ ጥናዊ ፅሁፎችን፣ መፃህፍትን በማንበብ ማወቅ ይችላል፡፡ ታሪኩ ለተውኔት ሲቀርብ ብሔረሰቡ ሊቀበለው የሚችል ያልተዛባ ቅደም ተከተልን ያዘለመሆን አለበት፡፡ ታሪክ በተውኔት ውስጥ ድርጊቶችን በማከል የነገሮችን ትክክለኝነት እና ትክክል ያልሆኑትን ይለያል፡፡

2.1.3.6 ሚና ክፍፍል

ሚና ማለት አንድ ወይም ከዛ በላይ ገፀ-ባህሪያት የሚወስዱት ድርሻ ነው፡፡ በተውኔት ውስጥ አንድ ገፀ-ባህሪ የተሰጠውን ድርሻበሚገባ ከተወጣ ተውኔቱ ላይ ያለውን ድርሻ እና ሌሎች ላይ መነቃቃትን ይፈጥራል፡፡ በተውኔት ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህሪዎች የተቀበሉትን ድርሻ በተገቢው እንዲወጡ የአንድ ገፀ-ባህሪ ሚናዉን በተገቢው መወጣቱ ሌሎቹ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል አነሱም ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡እንዲሁም ተውኔቱን በዝግጅት፣ በድርሰት፣ በገፅቅብ፣ በአልባሳት፣ በቁሳቁስ የተሳተፉ ባለሞያዎች የሚና ክፍፍላቸው ያቀርባሉ፡፡ ፋንታሁን እንግዳ፡፡ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ፡፡ሀ፡፡እስከ ፡፡ፐ፡፡ በተሰኘው መፅሀፍ እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

ተዋንያን የሚጫወቱበት ድርሻ ነው፡፡ የሰው ልጅ በእለታዊ

ህይወት የሚወጣውሚና እና ተዋናይ በመድረክ ላይ የሚተውኑት

ሚና ተብሎ በሁለት አብይ ክፍል ሊካፈልይችላል። በአጠቃላይ

የመድረክየትወናሚናታስቦበት ተጠንቶ ለመቅረቡ ተዋንያኑም

ተመልካቹም የሚረዱ ጉዳይ ሲሆን የማህበረሰባዊና ግለሰባዊ

ሚናዎች በእያንዳንዱግለሰብየመድረክ ወይም የመቀፀል

ችሎትየሚወሰን ይሆናል። (1993፣29)

የሰው ልጅ በምድር ህይወት የተለያዩ ድርሻዎች አሉት።ለምሳሌ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አባት የገቢ ምንጭ ካለው የቤተሰቡነም ወጪ የማሟላት ድርሻ አለበት፣ ሚስት የባሏን የገንዘብ አቅርቦት ወደ ምግብ እናወደ ቤት እቃ የማካፋፈል ድርሻ ትወስዳለች። ልጆች የመማር ድርሻ አላቸው። በመድረክ ተውኔት የሚተውኑ ተዋናዮች ሀላፊነትን ተቀብለው መወጣት ተውኔታዊ ሚና ነው። ። በትውፊታዊ ተውኔት የሚና ክፍፍል ድርጊቱን በሚከውነው ከዋኝ ከባህሉ ባለቤት ከሆኑ የማህበረሰቡ አባላት ጋር በሚኖረው የተውኔት ጊዜ እድሜን፣ ፆጻን፣ ሀይማኖቱን ግላዊ አስተሳሰብን የእውቀት ደረጃን ባማከለ መልኩ ያቀርባል። በትውፊታዊ ተውኔት የሚሳተፉ ተዋንያን ተውኔት ውስጥ ባላቸው የተሳትፎ መጠን ድርሻን ይወስዳሉ ።

2.2 የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት

አጥኚው ጥናታዊ ፅሁፍን የሚያጠናው የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በትውፊታዊ ተውኔት እሳቤ አስረጂነት ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ጥናታዊ ፅሁፎች እንደ ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝትነት ተጠቅሟል። ሰዋየሁ ለገሰ በ2010 ዓ.ም በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቲአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ‹‹ የኦሮሞ ጉጂ የጋብቻ ስነ-ስርአት ከቃለ-ተውኔት እና ከመቼት አንፃር›› በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው ።

የሰዋየሁ ለገሰ ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች የጉጂ ኦሮሞ የጋብቻ ስነ ስረአቶች ላይ ማተኮራቸው እና ባህላዊ ስረአቶች ላይ ትኩረት በማድረጋቸው ያመሳስላቸዋል ።

የሰዋየሁ ለገሰ ጥናታዊ ፅሁፍ እና ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚለያያቸው ነገር ደግሞ የሰዋየሁ ለገሰ ጥናት የጉጂ ኦሮሞ የጋብቻ ስነስርዓት ከቃለ ተውኔት ከመቼት አንፃር ነው ። በዚህም መሰረት ሁለቱ ጥናቶች በርእስ እና መረጃዎችን የሚተነትኑበት መንገድ ይለያያል ።

ሌላኛው ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያለው ጥናታዊ ጽሁፍ በምድራዊት እንዳለ በ2013 ዓ.ም በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቲአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ‹‹የሁሩ የቡሔ በአል አካባበር ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር›› በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። ምድራዊት እንዳለ በጥናቷ ስለ ሁሩ የቡሔ በአል አከባበር ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር በሚል ርዕስ በአራት ምዕራፎች ከፋፍላ ጥናታዊ ፅሁፏን አቅርባለች ።

ይህ ጥናት ከምድራዊ እንዳለ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም በአራት ምዕራፎች የተዋቀሩ ሲሆን ትውፊታዊ ተውኔትን መሰረት አድርገው ባህላዊ የሆኑ ስነ ስረአቶች ላይ በማተኮራቸው ነው ።

ይህ ጥናት ከምድራዊ እንዳለ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የሚለያያቸው ከርዕስ ጀምሮ የሚያጠኑበት ባህል እና መረጃ የሚተነትኑበት መንገድ ይለያያል ።

ምዕራፍ ሶስት

3. የመረጃ ትንተና

3.1 የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ መልካ ምድራዊ ዳራ

የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ደቡባዊ አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ሲሆን የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በሁለት ዞኖች ተከፍሎ ይኖራል። ዞኖቹም ምስራቅ ጉጂ ዞን እና ምዕራብ ጉጂ ዞን በመባል ይታወቃሉ። በምስራቅ ጉጂ ዞን 16 ወረዳዎች ሲኖሩ ፣ በምዕራብ ጉጂ ዞን ደግሞ 11 ወረዳዎች ይገኛሉ። የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በሚኖርበት ደቡባዊ የኦሮሚያ ክልል አካባቢ በድንበር የሚዋሰኑት ሌሎች ክልሎች እና ዞኖች ይገኛሉ። በምስራቅ የሱማሌ ክልል፣ በደቡብ የቦረና ዞን ፣ በምዕራብ የደቡብ ክልል ፣ በሰሜን የሲዳማ ክልል እና የባሌ ዞን ይዋሰኑታል። የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የገቢ ምንጭ የሆነው እና ህዝቡ ራሱን የሚያስተዳድረው ፣ በእርሻ በቆሎ እና ጤፍ በስፋት በማምረት ፣ የቀንድ ከብት እርባታ ፍየል ላምና በሬ በማርባት ፣ የዶሮ እርባታ ፣ የቡና ምርት ፣ ንብ ማነብ ፣ ንግድ ፣ እንስሳትን በማድለብ እና መሸጥ ፣ ማእድን በማውጣት በተለይም ወርቅ ቆፍሮ በማውጣት አጥቦ በመሸጥ ኑሮውን ይገፋል። ከወርቅ በተጨማሪ በጉጂ ዞን የሚገኙ ማዕድናት ፣ ታንታለም ፣ አይረን ፣ ንኬል ፣ ኮፐር ፣ ክሮማይት ፣ ፊልድ ፣እስፓሪ ፣ ማይካ ይገኛሉ።

የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ ህይቱን በመሰረተበት ደቡባዊ የኦሮሚያ ክልል ቆላ ፣ ደጋ ፣ ወይናደጋ ፣ የአየር ንብረት አለው። የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ ራሱን የሚያስተዳድረው በገዳ ስረአት ነው ። የገዳ ሰረአት በ11ኛው ክፍለዘመን የተጀመረና በዩኔስኮ የአለም ቅርስነት የተመዘገበ የዲሞክራሲ ስረአት ነው። በገዳ ስረአት ውስጥ አምስት ፓርቲዎች ይገኛሉ። ሙዳና ፣ ሀልቺሳ ዳለና ፣ ሀርሙፋ እና ሮበሌ ናቸው። በየስምንት አመቱ የስልጣን ርክክብ እየተደረገ ገገር የሆነው ተረኛ ፓርቲ በህግ ላይ ተመስርቶ ሰውን ፣ እንስሳትን ፣ ደኑን ፣ ወንዙን በገዳ ስረአት ያስተዳድራል። የገዳ ሰረአት ፓለቲካዊ ፣ማህበራዊ እና ሀይማኖታዊ ተቋማትን በውስጡ ያካተተ ስረአት ነው። (የአዶላ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ)

3.2 የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የጋብቻ ሰነ -አይነቶች

በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አራት አይነት የጋብቻ ሰነ - ስረአቶች አሉ። አዲባና (addi baana) ፣ ሐዋዲ (hawadii) ፣ ከዳ (kadhaa) ፣ ቡታ (butaa) ይባላሉ። በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ

የተመሳሳይ ጎሳ አባላት ጋብቻ መመስረት አይችሉም። በጉጂ ብሄረሰብ እድሜው ለጋብቻ የደረሰ ወጣት ከጋብቻው በፊት ራሱንቤተሰብ ለመመስረት የሚያበቃገንዘብ ሊኖረው ይገባል ፣ የብሄረሰቡን ባህል ጠንቅቆ ማወቅ አለበት ፣ በአካል ብቃት ጠንካራ መሆን ይገባዋል አቅሙን ለመፈተሽ ከእድሜ እኩዮቹ ጋር ትግል ገጥሞማሸነፍ አለበት። እነዚህን መመዘኛዎች ካሟላ ከራሱ ጎሳ ውጪ የሆነችን ሴት ማግባት ይችላል። በአራቱም የጋብቻ ስነስረአቶቹ ላይ የሚዘጋጀው ምግብና መጠጥ እንዲሁም የባህሉ መገለጫ የሆኑ ስነስረአቶች (ስጦታዎች) አንድ አይነት ናቸው ።የጋብቻው አይነት ቡታ (ጠለፋ) ከሆነ ገንዘብ እና ጊደር ተጨማሪ ያቀርባል ። በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በሴቶች ፍላጎት ላይ የተመሰረተው የጋብቻ ስነ - ስረአት አዲባና ሲሆን በራሷ እና በባህሉ መሰረት የምትፈልገውን ወንድ መርጣ ታገባለች።

3.2.1 አዲባና (addi baana)

የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አዲባና የገብቻ ስነ - ስረአት በሴቷ ፍላጎት ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው። ይህን የጋብቻ ስነ -ስረአት የምትፈፅም አንዲት የጉጂ ኦሮሞ ልጃገረድ ትልቅ ቦታ ይሰጣታል። ትከብራለች። የጋብቻ ስነ - ስረአቱ ሴቷ ወደ ወደደችው ወንድ ቤት በራሷ ፍላጎት በመሄድ ጋብቻውን ትፈፅማለች ። አልፎ አልፎ ልጁ ቤት የምትሄደው ገንዘቡን ፈልጋ ወይም ባል በማጣት ጊዜዋ እንዳያልፍባት አስባ ሊሆን ትችላለች ። ይህች ልጃገረድ የእውነት ፍቅር ካደረባት ወደ አፈቀረችው ወንድ ቤት ከመሄዷ በፊት የልጁን ጎሳ ታጠናለች በጎሳ አንድ ከሆኑ ጋብቻ መፈፀም ስለማይቻል። እንዲሁም የቤተሰቡን ሁኔታ ፣ የከብት በረት በየት በኩል እንደሆነ ፣ በአከባቢው ያለውን ፀባይ ፣ የስራ ታታሪነቱን ካጠናች በኋላ ራሳን ታዘጋጃለች። (ሚልኪ)የተባለች ወፍ ታዳምጣለች ፣የወፏ ጥቆማገዳም የሚሆነው (ሚልኪ) ከልጅቷ በስተግራ ከጮኸች ጥሩ እድል አለ ማለትነው በስተቀኝ ከጮኸች ጥሩ ያልሆነ ነገር ይፈጠራል ማለት ነው። ልጅቷ (ሚልኪ) አዳምጣ በግራ ከጮኸች ወደ ልጁ ቤት ለመሄድ የምቲዛቸውን ቁሶች እና አልባሳት ታዘጋጃለች። የምትለብሰው ሙሉ የጉጂ የሴቶች ቦሮ ፣ (ካሌ) ከቆዳ እና ከጨሌ የተሰራ የልጅ ማዘያ ፣ (ሳማጤ) በፀጉር ላይ ወደ ኋላ የሚንጠለጠል የልጃገረድነት ምልክት ከጨሌ እና ከቆዳ የሚሰራ ፣ (ሲቆ) ቀጭን ብትር ፣ ወተት በቅል ሞልታ ትይዛለች። ወደ ወደደችው ልጅ ቤት ትሄዳለች። የልጁን ቤት ባጠናችው መሰረት ከቤቱ ስትደርስ የያዘችውን (ሲቆ) ቀጭን ብትር ወደ ከብት በረት ትወረውርና የቤቱን በር በማንኳኳት በሩ ሲከፈት ለከፈተው ሰው ሰላምታ አቅርባ " የመጣውት በአዲባና ስነ - ስረአት ነው ልጃቹን ወድጀው መጥቻለው አስገቡኝ ትላለች ፣ በሩን የከፈተው የልጁ አባት ወይም እናት ከሆኑ የሚጠይቁት ጎሳዋን ፣ ስለቤተሰቦቿ የማን

ቤተሰብ እንደሆነች ይጠይቋታል። ልጅቷ አዚህ ከመምጣቱ በፊት የኛ ጎሳ ከእናንተ ጎሳ ጋር እንደሚለያይ አረጋግጫለው። የማን ቤተሰብ አባል እንደሆነች ትነግራቸዋለች።

ወደ ቤቱ ያስገቧታል የወደደችውን ልጅ መኝታ ትጠይቃለች ፣ የትኛው እንደሆነ ሲያሳዩዋት ሄዳ ትቀመጣለች። የልጁ ቤተሰቦች ልጃቸውን ለብቻው አስቀምጠውት አንተን የወደደች ሴት መጥታለች እና ተቀበላት በማለት ይነግሩታል ። ልጁ ባይወዳት እንኳን በቤተሰቡ ግፊትእንዲያገባት ይደረጋል ፣ በአዲባና ስነ - ስረአት የመጣች ልጃገረድ ሰላም ፣ጤና ፣ ፍቅር ፣ ደስታ ፣ ሀብት ፣ ይዛ ትመጣለች ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ልጅቷን መግፋት ትልቅ ነውር ተደርጎ ይታሰባል። ልጁ ልጅቷን ከወደዳት መስማማቱን ለመግለጽ የያዘችውን ወተት ይቀበላትና ለአባቱ ይሰጠዋል አባቱ ሁለቱንም መርቆ መጀመሪያ ለልጁ ከዛ ለልጅቷ ያጠጣቸዋል። የልጁ ቤተሰቦች ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ሽማግሌ በመላክ የሰርጉን ቀን ይቆርጣሉ ። በመጀመሪያ ቀን የሰርጉ ለት የሙሽራው ቤት ይደገስና ዘመድ አዝማድ ፣ ሁሉም ታዳሚ በተሰበሰበት የጋብቻው ስነ ስረአት ይካሄዳል ። በሁለተኛው ቀን የሙሽሪት ቤተሰቦች ጋር መጠነኛ ምግብና መጠጥ ተዘጋጅቶ ሙሽሮቹ እና የሙሽራው ቤተሰቦችን ቤታቸው ጋብዘው በጋራ አብረው ተመግበው ሙሽሮቹን መርቀው እርስ በእርስ በደንብ ተዋውቀው ይለያያሉ ።

ለድግሱ የሚዘጋጁ ምግብና መጠጦች እና ሌሎች ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

1. ቡና ቀላ ፦ ድፍን ቡና ተቆልቶ በቅቤ ተለውሶ በእንጨት ወይም በቀንድ ማንኪያ የሚበላ ባህላዊምግብ።.

2. ለምለም አበባ፦ የሙሽሮቹ ኑሮ የለመለመእና እንደ አበባ ያማረ እንዲሆን ምኞትን ለመግለፅ ያገለግላ።

3. ትንባሆ ፦ የባህሉየደስታ መገለጫ ስለሆነ ያስፈልጋል ።
4. ቦካ ፦ ከማር የሚሰራ መጠጥ በባህሉ መሰረት የደስታ መግለጫ መጠጥ ነው

5. ጭኮ ፦ ከገብስ ዱቄት እና ከቅቤ የሚሰራ ምግብ ።

የጋብቻ ስነስርዓት ላይ ሙሽራው አንድ ጊደር እና አቅሙ የፈቀደውን ገንዘብ ይዞ ይቀርባል ። እንዲሁም ለሙሽሪት አባት ኩታ ለእናት ነጠላ ያለብሳል ። ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ማድረግ ካልቻለ ሙሽሮቹ የቤተሰብ ምርቃት አያገኙም ።

3.2 2 ሐዋዲ (hawaddii)

የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ ከሚጠቀምባቸው የጋብቻ ስነ ስረአቶች መካከል ሐዋዲ በማጨት የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ነው። ሐዋዲ የጋብቻ የጋብቻ ስነ ስረአት አንድ የጉጂ ኦሮሞ ወጣት የወደዳትን የጉጂ ልጃገረድ የምትኖርበትን አከባቢ በማጥናት ቀርቦ በማግባባት ያነጋግራታል። ከየት ጎሳ እንደሆነች ፣ የቤተሰቧን ማንነት በማጥናት እና ቀርቦ ለጋብቻ እንደሚፈልጋት እና እነደምታገባው በማሳመን የግባባታል ፣ እሺታን እስኪያገኝ ድረስ መውጫና መግቢያ እየተከታተለ እያግባባ ያሳምናታል ። በሀሳቡ ተስማምታ ልታገባው ፍቃደኛ ከሆነች ወደ ቤቱ ይዟት ይኮበልላል። ቤተሰቦቹን አስቀምጦ ደበቆ ያመጣት ልጃገረድ እንዳለች እና ጋብቻ እንዲፈፀም ሽማግሌ እንዲልኩ አግባብቶ ይነግራቸዋል ። ቤተሰቦቹም የልጅቷ ጎሳ ከእነሱ ጋር እንደማይመሳሰል እና የቤተሰቧን ሁኔታ ካጣሩ በኋላ ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ሽማግዎች (አባ ገዳዎች) በመላክ ልጃቸው እነሱ ጋር እንዳለች እና ያለማንም አስገዳጅነት በገዛፍቃዷ ልጁን ልታገባው ወስና አብራው ወደ ቤቱ እንደሄደች አስረድተው መርቀው እንዲድሯት በማሳመን ጋብቻቸውም በቅርቡ እንዲፈፀም አግባብተው ያስረዳሉ ። የልጅቷ ቤተሰቦች በልጃቸው ምርጫ ነው ብለው ካሰቡ ጋብቻቸውን ይፈቅዳሉ ። የልጅቷ ቤተሰቦች እንዳይጋቡ ቢፈልጉም ጋብቻውን ማስቀረት ከባድ ስለሚሆንባቸው በሽማግሌዎችቹ ሀሳብ ይስማማሉ ። አብዛኛው ጊዜ ግን የልጅቷ ቤተሰቦች አማራጭ በማጣት ሳይሆ የልጃቸውን ፍላጎት በማክበር ጋብቻውን ይፈቅዳሉ ። ለጋብቻወ ሰነ ስረአቱ የሚያስፈልጉ ምግብና መጠጦች እንዲሁም የባህሉ መገለጫ የሆኑ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው ፦

1. ቡና ቀላ ፦ ድፍን ቡና ተቆልቶ በቅቤ ተለውሶ በእንጨት ወይም በቀንድ ማንኪያ የሚበላ ባህላዊ ምግብ።

2. ለምለም አበባ ፦ የሙሽሮቹ ኑሮ የለመለመ እና እንደ አበባ ያማረ እንዲሆን ምኞትን ለመግለፅ ያገለግላል።

3. ትንባሆ ፦ የባህሉየደስታ መገለጫ ስለሆነ ያስፈልጋል ።

4. ቦካ ፦ ከማር የሚሰራ መጠጥ በባህሉ መሰረት የደስታ መግለጫ መጠጥ ነው ።

5. ጭኮ ፦ ከገብስ ዱቄት እና ከቅቤ የሚሰራ ምግብ ።

ከተጠቀሱት በተጨማሪ አንድ ጊደር እና አቅሙ የፈቀደውን ገንዘብ ይዞ ይቀርባል ።
በተጨማሪ ለሙሽሪት አባት ኩታ ለእናት ነጠላ ያለብሳል ። ሙሽራው ይህን ማድረግ ካልቻለ የቤተሰብ ምርቃት አያገኙም ። ሙሽራው በሙሽሪት ቤተሰብ የተጠላ ይሆናል ።

3.2.3 ከዳ (kadhaa)

ከዳ የጋብቻ ስነስረአት በልመና የሚካሄድ ስነስረአት ነው ። ከዳ የጋብቻ ስነስርአት አንድ እድሜው ለጋብቻ የደረሰ የጉጂ ኦሮሞ ወጣት የወደዳትን ሴት ጎሳዋን ፣ የምትኖርበትን አከባቢ ፣ የቤተሰቧን ሁኔታ ፣ካጠና በኋላ እንደወደዳት እና ለጋብቻ እንደተመኛት እርግጠኛ ከሆነ በኋላ ለቤተሰቦቹ ማግባት እንደሚፈልግ እና ለትዳር ያሰባት ሴት እንዳለች ስለ ጎሳዋ ፣ ስለ ቤተሰቧ እንዳጠና አብራርቶ ያስረዳቸዋል። ቤተሰቡም በልጃቸው ሀሳብ ከተስማሙ ሽማግሌ (አባ ገዳ) ወደ ልጅቷ ቤተሰብ በመላክ በማስማማት እና በመለመን ለጋብቻ እንዲፈቅዱ ያደርጋሉ ። ሽምግልናው እሺታ ካገኘ ና የልጅቷ ቤተሰብ ልጃቸውን ለመስጠት ከተስማሙ ጋብቻቸው ይፈፀማል ። በጋብቻ ስነ ስረአቱ ላይ ምግብና መጠጥ ሌሎችም የባህሉ መገለጫ የሆኑ ነገሮች ይዘጋጃሉ ።

1. ቡና ቀላ ፦ ድፍን ቡና ተቆልቶ በቅቤ ተለውሶ በእንጨት ወይም በቀንድ ማንኪያ የሚበላ ባህላዊ ምግብ።

2. ለምለም አበባ ፦ የሙሽሮቹ ኑሮ የለመለመ እና እንደ አበባ ያማረ እንዲሆን ምኞትን ለመግለፅ ያገለግላል ።

3. ትንባሆ ፦ የባህሉየደስታ መገለጫ ስለሆነ ያስፈልጋል ።

4. ቦካ ፦ ከማር የሚሰራ መጠጥ በባህሉ መሰረት የደስታ መግለጫ መጠጥ ነው ።

5. ጭኮ ፦ ከገብስ ዱቄት እና ከቅቤ የሚሰራ ምግብ ።

በተጨማሪ ለሙሽሪት አባት ኩታ ለእናት ነጠላ ያለብሳል እንዲሁም አንድ ጊደር እና አቅሙ የፈቀደውን ገንዘብ ያበረክታል። ይህን ማድረግ ካልቻለ የቤተሰብ ምርቃት አያገኝም ። ሙሽራው መጀመሪያ የወደዳትን ልጃገረድ ለማግባት ሲወስን የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አሟልቶ ማድረግ ከቻለ ብቻ ነው ጥያቄውን የሚያቀርበው አቅም ከሌለው ቤተሰብም ልጁን አይሰጥም ።

3.2.4 ቡታ (buttaa)

ይዘጋ ቡታ በጠለፋ የሚፈፀም የጋብቻ ስነ - ስረአት ነው ። አንድ የጉጂ ወጣት ወንድ የወደዳትን ሴት መውጪያ መግቢያዋን አየተከታተለ ጎሳዋን በማጥናት ከሱ ጋር እንደማይመሳሰል ካረጋገጠ በኋላ ብቻዋን ስትሆን ጠብቆ ከልጅቷ ፍላጎት ውጪ በግድ በኃይል ተጠቅሞ ጠልፎ ወደ ቤቱ ይወስዳታል ። ከሁለት ቀን በኃላ ለቤተሰቦቹ አሳውቆ ሽማግሌ ይልካል ። የልጅቷ ቤተሰቦች አልፎ አልፎ ሽማግሌዎቹ ላይ ድብደብ ይደርሳል ። የሽማግሌዎቹ መደብደብ መደፈርን ለማሳየት ሲሆን ሽማግሌዎቹ ሁሉ ነገር ታጋሽ ሆነው አሳልፈው ነገሩ በሰላም እንዲፈታ ያደርጋሉ ። ጉዳዩ ከተካረረና በሽማግሌ የማለቅ ተስፋ ከሌለው ወደ ህግ ቦታ በመቅረብ በህግ ይዳኛሉ ። የተጠለፈችው ልጅ በህግ ፊት ቀርባ ልጁን መውደድ አለመውደዷን ተጠይቃ አልወደውም ተበድያለሁ ፍርድ ይሰጠኝ ካለች ልጁ በገንዘብ እና በእስር ይቀጣል ። በተቃራኒው ከሆነና ልጁን እወደዋለሁ ካለች የልጁ ቤተሰቦች እና የልጅቷ ቤተሰቦች እርቅ አድርገው ሙሽሮቹ ጋብቻቸውን እንዲፈፅሙ ይደረጋል ። አብዛኛው ጊዜ የተጠለፈች ሴት ልጅ ልጁን አልወደውም በግድ ነው የጠለፈኝ ብላ ቃሏን አትሰጥም ምክንያቱም ከዛ በኋላ ልጃገረድ አደለችም ተብላ ሰለምትታሰብ ባል የማግኘት እድል አይኖራትም ስለዚህ ያለችበትን ህይወት ወደደችውም አልወደደችውም እዛው መኖርን ትመርጣለች ። በሰርጋቸው ስነ ስረአት ላይ ምግብና መጠጥ እንዲሁም የባህሉ መገለጫ የሆኑ ነገሮች ጃሉ ።

1. ቡና ቀላ ፦ ድፍን ቡና ተቆልቶ በቅቤ ተለውሶ በእንጨት ወይም በቀንድ ማንኪያ የሚበላ ባህላዊ ምግብ።

2. ለምለም አበባ ፦ የሙሽሮቹ ኑሮ የለመለመ እና እንደ አበባ ያማረ እንዲሆን ምኞትን ለመግለፅ ያገለግላል ።

3. ትንባሆ ፦ የባህሉየደስታ መገለጫ ስለሆነ ያስፈልጋል ።

4. ቦካ ፦ ከማር የሚሰራ መጠጥ በባህሉ መሰረት የደስታ መግለጫ መጠጥ ነው ።

5. ጭኮ ፦ ከገብስ ዱቄት እና ከቅቤ የሚሰራ ምግብ ።

በተጨማሪም ሙሽራው ለሙሽሪት እናት ነጠላ ፣ ለአባት ኩታ ፣ ሁለት ጊደር ፣ ሀያ ሺህ ብር ይዞ መቅረብ አለበት የሙሽሪትን ቤተሰቦች ደስ ለማሰኘት አንዳንዴ የገንዘቡ መጠን ከፍ ሊል ይችላል ።

3.3.የአዲባና ጋብቻ ስነ-ስርአት በትውፊታዊ ተውኔት ምንነት

የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ ውስጥ ከሚገኙ አራት አይነት የጋብቻ ስነ-ስርአቶች ውስጥ አንዱ አዲባና ነው፡፡ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአትን ወደ ትውፊታዊ ተውኔት ለመቀየር በመሰረታዊነትባህሉ፣ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ ዘፈኖች፣ ውዝዋዜ፣ መቼት፣ የሚና ክፍፍል፣ የአመጋገብ ስነ-ስርአት ይጠቀማል፡፡ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ጋበቻ ሲሆን ስነ-ስርአቱ በሚከናወንበት ወቅት የተለያዩ መቼቶችን ይጠቀማል፡፡ በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ሂደት ወቅት ከታዳጊ ልጆች እስከ አዛውንቶች ይሳተፋሉ፡፡ ባህላዊ የሆኑ ስርአቶችን በዋናነት የሚፈፅሙት ሽማግሌዎች፣ በማህበረሰቡ ተቀባይነት እና ተሰሚነት ያላቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡

3.3.1መቼት

መቼት ማለት ቦታ ጊዜና ማህበራዊ እውነታ በውስጡ የያዘ የተውኔት አላባ ነው፡፡ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በሚከናወንበት ጊዜ የራሱ ቦታና ጊዜ አለው፡፡ በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት የሚፈፀመው ሴቷ ልጃገረድ በገባችበት ቤት አካባቢ በሚገኝ ሰፊ ቦታ ቀትር ላይ ነው፡፡ የልጁ ቤተሰብ ቤት ሰፊ እና ብዙ ሰው ማስተናገድ የሚችል ከሆነ እዛም ሊደረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በልጅቷ ቤተሰብ ቤት ድግስ ተዘጋጅቶ ከሰርጉ በሁለተኛው ቀን ሙሽራው፣ ሙሽሪት የልጁ ቤተሰቦች ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ቤት በመሔድ የቤተሰብ ትውውቅ ያደርጋሉ፡፡ ስነ-ስርአቱ የሚከናወንበት ቦታ የተመረጠበት ምክንያት አቶ ፈይሳ ደበሌ እንደሚከተለው ያስቀምጣል ፡፡

አዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በልጁ ቤት በዋናነት

የሚከናወነው ልጅቷ ወዳው በአዲባና ስርአት ቤተሰቡን

ስለ ተቀላቀለች ጋብቻቸው እዛው ቤት ይከናወናል፡፡

በልጅቷ ቤተሰቦች ቤት ሽማግሌዎችን ለማስተናገድ

እና የሙሽራውና የሙሽሪት ቤተሰቦች መተዋወቂያ

በመሆንና ዝምድናን ለማጠንከር ያገለግላል፡፡ (ቃ.መ ፣ 01/09/2014)

3.3.2 ቁሳቁስ

ቁሳቁስ የሰው ልጆች በየ እለት ተእለት ክንውናቸው የሚጠቀሙባቸው ረዳት አገልጋዮች ናቸው፡፡ ቁሰቁሶች በጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ውስጥ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በሚከወንበት ጊዜ ቁሳቁሶች ከግልጋሎት ባለፈ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ፡፡ አጥኚው የአዲባና ስነ-ስርአትላይ በተመለከተው መሰረት የቁሳቁሱን ሚና እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

ቀጭን ብትር ለአዲባና የጋብቻ ስነ ስረአት ሴቷ የምትይዛት ብትር ፣

ቆራሱማወይም ወደ ልጁ ቤት የምትገባው ልጃገረድ ሲቆ እናወተት

በቅል መያዟ የአዲባና ስነ-ስርአትመሆኑን ይናገራል፡፡

ሽማግሌዎች (አባገዳዎች)የሚዙት ብትር ወይም የገዳ በትር፣

ቤት ውስጥ የሚጠቀሙባቸው የመመገቢያና የመጠጫ

እቃዎች፣ የሸክላ ድስት፣ የእንጨት ወይም የቅልሳህን፣

የቀንድ መጠጫ፣ ከቀንድ ወይም በእንጨት የሚዘጋጅ፣ማንኪያ፣

የሸክላ የቡና ምጣድ፣ውሃ ማስቀመጫ ጋን ከሸክላ የተሰራ፣

አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ (ምልከታ ፣ 12/12/2013)

በጉጂኦሮሞ ብሔረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ውስጥ ልጃገረዷ ወደ ልጁ ቤት ስትሔድ (ሲቆ)የሚባል የወይራጭስ በታጠነቅልሚኢትኩስወተትበመያዝለጋብቻ እንደ መጣች ይጠቁማል፡፡ ልጃገረዷ የወደደችው ወንድ ቤት ገብታ የተወደደውወንድልጅ በቅል የያዘችውን ወተት ከተቀበላት እንደሚያገባት ያረጋግጣል፡፡ ሽማግሌዎቹ (አባ ገዳዎች)የሚዙት የገዳ ብትር በእድሜ ከፍ ማለታቸውን ፣በገዳስረአት ውስጥየስልጣንደረጃቸውንለመለየት ይረዳል፣ እንዲሁምበህዝቡ የተከበሩ መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች፣ የሸክላ ድስት፣ የቀንድ ወይም የእንጨት ማንኪያ፣ ቅቤ፣ ድፍን ቡናየሸክላ ምጣድ፣ ማብሰያ እንጨትቡና ቀላ ለማዘጋጀት እና ለመመገብ ያገለግላሉ፡፡ የገብስ ዱቄት በዛ ያለ ቅቤጭኮ ለማዘጋጀትያገለግላሉ ፡፡ ማር ፣ ውሃ፣ ጌሾ ቦካ ለማዘጋጀትያገለግላሉ ፡፡ ቁሰቁስበአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ወቅት በዘፈን ውስጥ አሉ፡፡

ወጣቶች ሶስት ቀጫጭን ረዘም ያሉ እንጨቶችን በጋራ በመያዝ እና ፊሽካበአፋቸው እየነፉ ሰርጉን ያደምቁታል፡፡ በሌላ በኩል ሰርጉላይ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችለምለም አበባ፣ ትንባሆ፣ የሙሽራው አቅም የፈቀውገንዘብመጠንይቀርባል፡፡ ለምለም አበባ የደስታና የምኞትን መግለፅ ስለሚችል በስነ-ስርአቱ ላይ ይኖራል፡፡ትንባሆ የባህሉ መገለጫ ስለሆነ ይቀርባል፡፡ የሙሽራውአቅምየፈቀደውንገንዘብለልጅቷ ቤተሰቦች በስጦታ ያበረክታል፡፡

3.3.3 ግብአተ ድምፅ

በጉጂኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ ግብአት ድምፆች አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ በጋብቻ ስነ-ስርአቱ ላይ ባህላዊ የሆኑ የማጀቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ሰርጉን ያጅባሉ፡፡ መምህር ንጉሴ እሼቱ በአዲባና ስነ-ስርአት የግብአት ድምፅ ሚናንእንደሚከተለው ያስረዳል ፡፡

ለሰርጉ መጀቢያ የሚያገለግሉ የባህላዊ መዚቃ

ማሳሪያዎች በአቅራቢያ የሚገኙ ቀጫጭን እንጨቶች ወይም

በእጅ የሚያዙ የገዳብትሮች፣ ፊሽካ፣ የእጅ

ጭብጨባ፣ ሁለት አጫጭር እንጨቶች በማጋጨት፣አነስተኛ ከበሮ በአንድ

እጅ በመምታት ከሰርጉ ማጀቢያ ይጠቀማሉ፡፡ (ቃ.መ 01/09/2014)

ወንዶች ጎን ለጎን በመሆን የሚዙት የገዳ ብትር ወይም በአቅራቢያ የተገኙሶስት ቀጫጭን እንጨቶች በአንድ ላይ በማድረግ በአንድ እጃቸው ሶስት ወይም ከዛ በላይ ሆነው በመያዝ በሌላ እጃቸው በሚሂት ቀጭን ብትር እኩል ወደ ላይ እየዘለሉ እንጨቱን እየመቱ የሚወጣውንድምፅእንደ ማጀቢያበመጠቀም ይጨፍራሉ፡፡ ሴቶች እጃቸውን ወደ ግራ ቀኝ እያወዛወዙ በመሀል እያጨበጨቡ እንዲሁም ሁለት አጫጭር እንጨቶች በመያዝ እርስ በእርስ ያጋጫሉበተጨማሪምሴቶችበአንድ እጅ የምትያዝከሸክላ እና ከቆዳ የተሰራች አነስተኛ ከበሮ በግራእጃቸው በመያዝ በቀኝ እጃቸው ከበሮን እየመቱየዜማውን ፍሰት ጠብቀውግብአተ ድምፆችን ይፈጥራሉ ፡፡

3.3.4 አልባሳት

አልባሳት በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ የአልባሳት ሚና ሰውነትን ከመሸፈን በተጨማሪ የክብር፣ የጋብቻ ፣የወደፊት ምኞትን፣ የኑሮ ደረጃን ይገልፃል። አቶ ሰለሞን ዋቆበአዲባናአልባሳት ያላቸውን ሚናእንደሚለውይገልፀዋል።

ልጁ ቤት የምትገባው ልጃገረድ ሙሉ የጉጂየሴቶች

ቦሮትለብሳለች፣ ጀርባዋ ላይ የልጅ ማዘያ (ካሌ) ከቆዳና ከጨሌ

የተሰራ ትለብሳለች፣ በፀጉር ላይ የሚንጠለጠል (ሳማጤ)

የልጃገረድነት ምልክት ትለብሳለች፣ ሽማግሌዎች

(አባገዳዎች) ሙሉ የጉጂኦሮሞ ቦሮ ይለብሳሉ።

ሙሽራው ለሙሽሪት ቤተሰቦች ስጦታ ያበረክታል።

ለአባት ኩታ ለእናት ነጠላ ያለብሳል። (ቃ.መ 03/09/2014)

በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ ወደ ልጁ ቤት የምታቀና ሴት ሙሉ የጉጂየሴቶች ቦሮ ትለብሳለች ። ቦሮ በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ ባህልን የማክበር ማሳያ ነው።የጉጂ የሴቶች ቦሮ ነጭ አላባሽ እና ነጭ ቀሚስ በመልበስ በላዩ ላይሙሉነጭሆኖ አግድም ጥቁር መስመሮች የተሰመሩበት ልብስ ከትከሻቸው እስከተረከዛቸው ድረስ ይወርዳል ። ልጃገረዷ በጀርባዋ ላይ ከቆዳ እና ከጨሌ የተሰራ የልጅ ማዘያ (ካሌ) ትለብሳለች። በታዘለችው ካሌ ትዳር ለመመስረት እና ወደ ፊት በትዳርህይወቷ ልጆች እንደሚኖሯት ተስፋን ይዛ እንደ መጣችያሳያል።ይዛ የምትመጣው ካሌ ለምልክት ወይም የትዳር ፍላጎቷን ለመጠቆም ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት በትዳር ህይወቷ ተሳክቶላት ልጅ ካፈራች ልጁን ለማዘያነት ትጠቀምበታለች።የጉጂ ልጃገረዶች በአንገታቸው ላይየሚያደርጉት ጨሌ በወፍራም ክር ውስጥ ገብቶ የተሰራ ሲሆን በአንገታቸው ላይ ሲያስገቡ እስከ ደረታቸው ድረስይን ጠለጠላል ።

ወደ ልጁ ቤት የምትገባው ልጃገረድ በፀጉሯ ላይ አድርገው ወደ ኋላ የሚንጠለጠለው (ሳማጤ) የልጃገረድነት ምልክት መሆኑና ክብሯንየጠበቀች መሆኗንያሳያል።ሳማጤሁለት አይነት ሲሆን ልጃገረድ ሴቶች የሚያደርጉት እና የጉጂ እናቶች የሚያደርት ነው። በቀጭንቆዳ ላይ ጨሌዎች

በተለያዩ ቀለማት ተደርድረው ይሰፉበትና ልጃገረድ የሆኑ ሴቶች በፀጉራቸው ላይ በማድረግ ከግንባራቸው ጀምሮ ወደኋ ላበፀጉራቸው ላይ ዞሮአስከማጅራታቸውድረስያንጠለጥሉታል ። እናቶችየሚያደርጉትሳማጤየፀጉርንየላይኛውክፍልየሚሸፍንሲሆን የሚሰራውቆዳ እርስ በእርሱ እየተደራረበ እንዲያያዝበማድረግ ወደ ኋላ በቀጭን ቆዳ እንዲወርድ ተደርጎ ይዘጋጃል። በጋብቻ ስነ-ስርአቱ ላይ ሙሽራው፣ ሚዜዎቹ ሽማግሌዎች(አባገዳዎች) የሚለብሱትሙሉ በሙሉ ነጭ ሲሆን ረዘም ያለቁምጣጫፉ ላይ ቀጭን ቡኒ መልክ ያለው ጥለት ይኖረዋልእና አላባሽ ከላይ ተደርጎ በላዩ ላይ ሙሉ ነጭ ሆኖ ጫፉ ላይ ቡኒ ጥለት በቀጭኑያለው ጋቢ ይደረባል። ከጥጥ የሚዘጋጀውሙሉ ነጭ የሆነውየጉጂ ኦሮሞ የወንዶች ቦሮ ለባህሉእንዲሁም ለብሄረሰቡ የክብር መገለጫ ነው። ሙሽራው ለሙሽሪት አባት በስጦታ የሚያበረክተው ኩታበብሄረሰቡ ዘንድ የክብር ምልክት ስለሆነ ሙሽራው አክብሮቱን ለመግለፅ ያበረክታል። ለሙሽሪት እናት ሙሽራው ነጠላ የሚያበረክተው ለአክብሮት እና ፍቅርን ለመግለጽ ነው። ሌላው በጋብቻ ስነ-ስርአቱ ላይ የሚሳተፉ ታዳሚዎች አቅማቸው የፈቀደውን አለባበስ ለብሰው ይገኛሉ።

3.3.5 ውዝዋዜ

ውዝዋዜ በጉጂኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ አገልግሎት አለው። በአዲባና ስነ-ስርአት ውዝዋዜ የውስጥ የደስታ ስሜትን ከመግለፅ ባሻገር አዳዲስ ጥንዶች የሚተዋወቁበትቀጣይ ሙሽራ የመሆን አጋጣሚንይፈጥራል።አዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት በሚካሄድበት ጊዜ ወጣቶች የብሄረሰቡን ውዝዋዜ ባህላዊ ዘፈኖችንእና ባህላዊ የሆኑ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሰርጉን ደስታ አብረው ይካፈላሉ። አቶፈይሳ ደበሌ በአዲባና ስነ-ስርአት ስለ ውዝዋዜ የሚከተለውን አስፍሯል።

በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በአዲባና ስነ-ስርአትም ሆነ በሌሎች

የጋብቻ አይነቶች የጉጂኦሮሞብሄረሰብውዝዋዜ አንድ አይነት ነው።

በጋብቻ ስነስርዓት ላይ ወንዶች ሶስት ረዘም ያሉ እንጨቶችን በጋራ

በመያዝ ወደ ግራ ወደ ቀኝ እያሉ ሲጨፍሩ ሴቶች ደግሞ ከወንዶቹ

ትይዩ ፊት ለፊት ሆነውእጃቸውን በደረታቸው ልክ አየር ላይ አድርገው

ወደ ግራና ወደ ቀኝ እያደርጉ በመሀልእያጨበጨቡ ይጨፍራሉ።

(ቃ -መ ፣ 01/09/2014)

በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ ወንዶች ሶስት እንጨቶችን በመያዝ እኩል ወደ ግራና ቀኝ ከወገባቸው እጥፍ እያሉ ይጨፍራሉ፡፡በተጨማሪ ወንዶች ብትር በእጃቸው ተደግፈው በአፋቸው ፊሽካ እየነፉ ከሴቶች ጋር ፊት ለፊት በመሆን ከወገባቸውዝቅ በማለት አንገታቸውን ወደ ግራና ቀኝእያወዛወዙበፉክክር መንፈስ ይጨፍራሉ፡፡ አንድለአንድ ውዝዋዜንወንዶችሴቶችን ለመማከር እናከሌሎችየተሻለ ሆኖለመታየትይጠቀሙበታል ፡፡ሴቶች ከወንዶቹ ትይዩ ሆነው በጋራ እኩል ተደርድረው ወደግራናቀኝእየተወዛወዙየጨፍራሉ ፡፡ አንድ ለአንድየሚደረገውጭፈራላይሴቶችበአብዛኛውበወንዶች ተጋብዘው ይጨፍራሉ ፡፡

3.3.6 ሚና ክፍፍል

ሚናማለትድርሻሲሆን፤ በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ወቅት ስነ-ስርአት ተጀምሮ እስኪያልቅሙሽሮች፣ቤተሰብ፣ሽማግሌዎች(አባገዳዎች)፣የሙሽራውጎረቤቶችሁሉምየራሳቸው ድርሻ አለው፡፡ አቶ ሰለሞን ዋቆየአዲባና የጋብቻ ስበ-ስርአት ላይ የሚና ክፍፍልን እንደሚከተለው ይገልፃል፡፡

ወደ ልጅ ቤት የምትገባው ልጃገረድ ቤቱ ገብታ

ለወደደችው ልጅ ወተቱን እስክትሰጠው ድረስ

የማስማማቱን ድርሻ የሚወስዱት የልጁ ቤተሰቦች

ናቸው፡፡ ሽማግሌዎቹ(አባገዳዎች) ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች መልዕክት

አድርሰው የሰርጉን ቀን የማስተካከል ድርሻ አላቸው፡፡

በሽማግሌዎቹ አማካኝነትሁለቱንም ቤተሰብ ያማከለ ቀን

ተቆርጦ ለሰርጉ ዝግጅት ይደረጋል ፡፡ የልጁ

ቤተሰቦች ለድግሱ ራሳቸውን የማዘጋጀት

ድርሻ አለባቸው፡፡ የልጁ ቤተሰብ ዘመዶች ሰርጉ

ላይ አቅማቸው የፈቀደውን ድርሻ ይወጣሉ፡፡ (ቃ-መ፣03/05/2014)

በጉጂኦሮሞ አዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ የልጁ ቤተሰቦች ትልቅድርሻ አላቸው ቤታቸው የመጣችውን ልጃገረድ ልጃቸው አልፈልጋትም እንዳይልና በብሔረሰቡ እንዳያስወቅሳቸው የማሳመን ድርሻ አለባቸው ።ሽማግሌዎች (አባገዳዎች)ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ከልጁቤተሰብተልከውየሰርጉን ቀንሁለቱን ቤተሰብሊያስማማየሚችልቀንይቆርጣሉበተጨማሪ የሰርጉሁኔታበምን መልኩ መሄድ እንዳለበት ከቤተሰብ ጋር በመነጋገር የስረአቱን ቀደም ተከተል ጠብቀው የመስኬድ ሀላፊነት አለባቸው ።የልጁ ቤተሰቦች የገንዘብ አቅም ካላቸው በራሳቸው መደገስ ይችላሉ ። አቅም የሚያንሳቸው ከሆነ ዘመድ አስተባብረው ድግሱን ይደግሳሉ።

ሽማግሌዎች (አባገዳዎች) ከልጁ ቤተሰብ ተልከው ወደ ልጅቷ ቤተሰብ በመሔድ የሰርጉን ቀን ሲወስኑ በአብዛኛውየልጁን ቤተሰብ ባማከለ መልኩ ግምት ውስጥ አስገብተው ቀንያመቻቻሉ ። ለሰርጉ የተቆረጠው ቀንበልጁ ቤተሰብ ላይ ጫና እንዳይፈጥርይደረጋል ምክንያቱም የጋብቻ ስነስረአቱ ዋነኛ ከዋኞች ሰለሆኑ ነው።ጊዜው እህል የሚሰበሰብበት ወቅት ካልሆነ ቤተሰቡ ጥሩ የገንዘብ አቅም በሚኖረውጊዜ ላይ ሰርጉ እንዲካሄድ የማድረግ ድርሻ የሽማግሌዎች(የአባገዳዎች) ይሆናል ። እንዲሁም የድግሱን ሁኔታ ተለታትለው፣ የሰርጉንም ሁኔታ በምርቃት ከፍታው ስነ-ስርአቱን አካሂደው መጨረሻ ላይ በምርቃት የማጠናቀቅ ሚናየሽማግሌዎች(የአባገዳዎች) ነው ።

3.3.7 የመጠጥእና የአመጋገብ ስነ-ስርአት

በጉጂኦሮሞ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ-ስርአት በሚካሁድበት ወቅት የራሱ የመጠጥና የአመጋገብ ስነ-ስርአት አለው። በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ ካሉት አራት አይነት የጋብቻ ስነ-ስርአቶች የመጠት እና የምግብ ዝግጅት በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአትየአመጋገብ እና የመጠጥ ስነ-ስርአት ለየት የሚልበት የተወሰነ ለውጥ አለው። አጥኚውየአዲባና ስነስረአት ላይ የመጠጥና የአመጋገብ ስነ-ስርአት የሚከተለውንተመልክቷል።

ወንዱ ልጅ ቤት የምትገባው ልጃገረድ በቅል የምቲዘው

ወተት ከሌሎቹ የጋብቻ አይነቶች፣ ቡታ፣ ከዳ፣

ሐዋዲ፣ ከእነዚህ ለየት ባለ መልኩ ነው ።

የሚጠጣው ልጁ ተቀብለው ለአባቱ ይሰጠዋል አባቱም

መርቆ መጀመሪያ ለልጁ ከዛ ለልጅቱ ያጠጣታል።

በሰርጉ ላይ የሚዘጋጁ ምግቦች ቡና ቀላ ጭኮ

ዋነኞቹ ናቸው። ከመጠጥ፣ ቦኮ፣ ወተት ይዘጋጃል። (ምልከታ፣12/12/2013)

በጉጂኦሮሞ ብሄረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ ወተት ትልቅ መልዕክት አለው አንድ የጉጂወጣት በአዲባና ስነ-ስርአት ቤቱ ገብታ አልጋው ላይ ወተት ይዛ የተቀመጠችን ሴት ወተቷን መቀበል አገባሻለው ማለት ነው። (ቡና ቀላ) ድፍን ቡና ጫፍ ላይ እየተበሳ ይቆላል፣ በደንብ ከበሰለ በኋላ በቅቤ ይለወሳል። ይህ ምግብ ከቀንድ ወይም ከእንጨት በተሰራ ማንኪያ ይበላል። (ቦካ) ከማር ፣ ከውሃናከጌሾየሚሰራ የደስታ መግለጫ መጠጥ ነው። ወተት በቅል እየተደረገ ይቀርባል። ጭኮ ከገብስ ዱቄት እና ከቅቤ ይዘጋጃል። ቡና ቀላ፣ ጭኮ፣ ቦኮ፣ ወተት፣ በሙሽሮቹ ፊት ይቀርባሉ። በመጀመሪያ ሽማግሌዎቹ(አባገዳዎቹ)ወተቱንእናቦካውን አንስተው ይመርቁናአንደ ተጎንጭተው ከቀመሱ በኋላ በሁለተኛውበአፋቸው በመሙላት ወደ ሙሽሮቹ፣ ወደ ቤተሰብ፣ ዘመድ ወደ ታዳሚው በአፋቸው ይረጩታል። ከዛም ምግብና መጠጡን በየተራ እያነሱ ከመረቁ በኋላ እየቀመሱ ለሙሽሮቹ ለሚዜዎቹ፣ ለቤተሰብ፣ ለዘመድ፣ ለጎረቤት፣ ለታዳሚው በሙሉ በቅደም ተከተል እንዲደርስያደርጋሉ ።

3.3.8 ዘፈን

በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ የዘፈን አገልግሎትበሰፊው አለ ። በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ ወጣቶች ተሰብስበው ሴቷ ሙሽራ ላይ ትኩረት አድርገው ይዘፍናሉ።ሰለሞን ዋቆ ስለ አዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ዘፈን ያለውን አገልግሎት እንደሚከተለውይናገራል ።

በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ የሚዘፈኑ

ዘፈኖች ሴቷ ሙሽራ ላይትኩረቱን አድርጎ

ስለ ቤተሰብ ፣ ሰለ ጉጂ አቃፊነት የሚያተኩሩ ናቸው።

በተጨማሪወጣቶች በጋራ ሆነው በሚጨፍሩበት ጊዜ

ለመ·ሸራው እናለቤተሰቡ መ·ገሳንእያስገቡይዘፍናሉ።

ከሚዘፈኑት ዘፈኖች ውስጥአንደ ምሳሌእንደሚከተለው ሰፍሯል ።

''Durra Adiibaana

Eebbifaamtuu Hintala

Kabbajashee Eegatte

Kanbonsiiiftee warra

Addashee kanbeektuu

Ulfiinaishe kaneegduu

Silaa kan guddissee Gujii

Gujii beeka safuu

Gujiin beeka tokkuummaa

Gujii beeka jalaala'

''Durra Aduubaana

Eebbifaamtuu Hintala

Kabbajashee Eegatte

Kanbonsiiiftee warra

Addashee kanbeektuu

Ulfiinaishe kan eegduu

Silaa kan guddissee Gujii

Gujii beeka safuu

Gujiin beeka tokkuummaa

Gujii beeka jalaala''

''አዲባና የጉጁ ሴቶች የነፃነት ማሳያ

የአዲባናዋ እንስት

የፍላጎት ተምሳሌት

የፍቅር ባህላችን መገለጫ

የጉጂዋ ቆንጆ

ሰራች አዲስ ጎጆ
ክብሯን የጠበቀች
ቤተሰብ ያኮራች
ጨዋ ወልዶ ያሳደጋት
ትታይ ባደባባይ
ጉጂ የመቻቻል የአብሮነት የፍቅር
የእኩልነት የነፃነት ምድር " (ቃ.መ 03/05/2014)

በአዲባና የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ በዘፈኖች ውስጥ ሙሽራዋ በተለየ ሁኔታ የምትሞገሰው በአዲባናየጋብቻ ስነ-ስርአት ወደ ልጁ ቤት የምትገባ ሴት በብሔረሰቡ ለሴቶች ያለውን የፆታእኩልነትበማንፀባረቁ ብሄረሰቡ የሰጣትን መብት በመጠቀሟ ለሌሎች እንደ አርአያ መሆን ስለምትችል እንዲሁም ፍላጎቷን በግልፅ በማድረጓ ትከበራለችበሰርጓ ላይም የተለየ ሙገሳ ታገኛለች ። በጋብቻ ስነ-ስርአቱ ላይ ወጣቶች ተሰብስበው ሙሽሪትን፣ ሙሽራውን፣ የሁለቱን ቤተሰቦች እዛው በተሰበሰቡበት ግጥሞችን እየፈጠሩ ባህላዊ ጭፈራዎችን በማከልየሰርጉን ስነ-ስረአት ያደምቁታል። በጉጂ የአዲባናየጋብቻ ስነስረአት ላይ የሚዘፈኑ ዘፈኖች መልዕክታቸው ለማን እንደሆነ ለምን እንደሚዜሙ አላማቸው ይታወቃል እንጂ የግጥም ገደብ የለውም በሰርጉስነ ስረአትላይ የሚታደሙ ተሳታፊዎች በነፃነትየሙገሳ ግጥሞችን እየጨመሩ መዝፈን ይችላሉ ።

ምዕራፍ አራት

4.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በጉጂ ኦሮሞ ብሄ ረሰብ የአዲባና የጋብቻ ስነ ስርዓት በምን መልኩ እንደሚካሄድ ፣ በማን እንደሚካሄድ ፣ ምን እንደሚካሄድ ፣ የሚካሄድበት ቦታ (መቼት) ፣ አልባሳት ፣ ቁሳቁስ ፣ ግብአተ ድምፅ ፣ ውዝዋዜ ፣ መጠጥ እና አመጋገብ ፣ ዘፈን ፣ የሚና ክፍፍልን ፣ በባህሉ ውስጥ ስነስርዓቱ እንዴት በትውፊታዊ ተውኔት ላይ እንደሚውል ለማሳየት ሞክሯል ። የአዲባና የጋብቻ ስነስርዓት በክዋኔው ሂደት ውስጥ የመከወኛ ቦታ (መቼት) ፣ የተመረጠበት ምክንያት በአዲባና ስነስረአት ሴት ልጅ በገባችበት ቤት እንደሆነ ይጠቁማል። አልባባሳት የወንድም የሴት ቦሮ በስነ ስረአቱ ላይ በስፋት ይለበሳል ። በተለይም በአዲባና ስነ ስረአት ወንዱ ቤት የምትገባው ሴት ሳማጤ ፣ ካሌ ፣ በእነዚህ አልባሳት የአንዲትን ሴት ማንነት መለየት ያስችላል። ቁሳቁስ በአዲባና የጋብቻ ስነስርዓት ውስጥ አንዲት ሴት ሲቆ ፣ ወተት በቅል መያሟ ብቻ ለአዲባና የጋብቻ ስነስርዓት መዘጋጀቷን ይጠቁማሉ ። ግብአተ ድምፅ ፣ የተለያዩ ባህላዊ መሳሪያዎች በመጠቀም የአዲባናን ስነ ስረአት ያደምቃሉ ። ውዝዋዜ ጋብቻው ከማድመቅ በተጨማሪ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶች የመተዋወቂያ መንገድ በመሆን ያገለግላል ። መጠጥ እና ምግብ በአዲባና የጋብቻ ስነ ስረአት ላይ በስፋት ይዘጋጃል ። ቡና ቀላ ፣ ጭኮ ፣ ተመራጭ ምግቦች ናቸው ፤ ቦሳ ፣ ወተት በስነ ስረአቱ ላይ ለመጠጥነት ይቀርባሉ ። ዘፈን በስነስርዓቱ ላይ የሚሳተፉ ወጣቶች እዛው በሚፈጥሩት ማወደሻ ግጥሞች ይጫወታሉ ። የሚና ክፍፍል በአዲባና የጋብቻ ስነስረአት ላይ ሙሽሮች ፣ ቤተሰብ ፣ ሽማግሎች (አባ ገዳዎች) ሰፊ ሚና ይወስዳሉ ።

በአጠቃላይ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ የጋብቻ ስነ ስረአቶች በተለይም ስለ አዲባና የጋብቻ ስነስርዓት እንዲሁም በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ያሉትን አላባውያን በጥናቱ ውስጥ ተንትኗል ።

4.2 የመፍትሔ ሀሳብ

የጉጂ ኦሮሞ ጋብቻ ብሄረሰብ አዲባና የጋብቻ ስነስረአት ለሴቶች መብትን ያጎናፀፈ ቢሆንም ባህሉ ከታለመለት አላማ ውጪ የገንዘብ ስነስረአት እየሆነ ነው ። ባህሉ ያለውን የመብት ነፃነት በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ለግል ጥቅም እየዋለ ነው ። አንዲት ሴት ባህሉን ሰበብ በማድረግ ገንዘብ ያለውን ወንድ በማጥመድ ባህሉን ተጠቅማ እንዲያገባት ታደርጋለች ። አዲባና የጉጂ ብሄረሰብ ለሴቶች ያለውን ከበሬታ ና ፍቅር የሚያሳይ ባህል ሆኖ ሳለ ትውፊታዊ ይዘቱን ባለመረዳት ገንዘብን በመሻት ባህሉ እየተመረዘ ነው። በብሄረሰቡ መሀከል የሚገኙ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ማጥራት ያስፈልጋል ። ስለአዲባና የጋብቻ ስነስረአት መዛህፍት ፣ፊልም እንዲዘጋጅ በማድረግ ባህሉ አንዲታወቅ ማድረግ ።

ዋቢ መፃህፍት

ፋንታሁንእንግዳ ። (1993)።ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ።አዲስ አበባ ። ብረሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ።

አለም እሸቱ ። (1994)።መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ።አዲስ አበባ። ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የልብራል አርትስ ፋካልቲ ህትመት ።

ያለውእንዳወቀ ። (2009) ። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር።አዲስ አበባ ። ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት ።

ዘሪሁን አስፋው ። (2005) ። የስነፅሁፍ መሰረታዊያን ። አዲስ አበባ ።ንግድ ማተሚያ ድርጅት ።

አዲስአለም አስቻለው ። (2010) ።ንግስት ዘውዲቱ ታሪካዊ ተውኔት ። አዲስ አበባ ። ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት ።

ሳሙኤል ተስፋዬ ። (2012) ። የመድረክ ጀርባ ጥበባት ። አዲስ አበባ ማይቢቲ ማተሚያ ቤት ።

አባሪ

የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

ስም	ፆታ	አድራሻ	ስራ	መረጃ የተሰጠበት ቀን
ንጉሴ እሼቱ	ወንድ	አዶላ ወዩ ከተማ	መምህር	01/09/2014
ፈይሳ ደበሌ	ወንድ	አዶላ ሬዴ ወረዳ	አርሶ አደር	01/09/2014
ሰለሞን ዋቆ	ወንድ	ኢርባ መዳ	አርሶ አደር	03/09/2014



በቅቤ የተዘጋጀ ቡና ቀላ



በቅቤ እና በገብስ ዱቄት የተዘጋጀ ጨኮ




የልጅ ማዘያ ካሌ ላይ ወተት በቅል ያዘለች የጉጂ ኦሮሞ ልጃገረድ



ሳማጤ እና ሙሉ የጉጂ ኦሮሞ የልጃገረዶች አለባበስ የለበሰች ሴት









የወተት ቆሎች



የልጁ አባት ወተት እያጠጣቸው



የወንዶች ውዝዋዜ



የሴቶች ውዝዋዜ



አባ ገዳዎች (ሸማግሌዎች)



የጉጂ ኦሮሞ እናትና አባቶች አለባበስ የለበሱ የብሄረሰቡ አባላት